የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

ግንቦት 13/2006

# የሱዳን ጸረ ኢትዮጵያውያን ግፍ እየቀጠለ ነው !

እውነቱን ለመናገር የተቃውሞና የማጋለጡ እንቅስቃሴ ደካማ ነው ። ትላንት ትላንት ወዲያም ቢሆን የሱዳን ፖሊሶች ኢትዮጵያዊ ስደተኞችን ማፈሱን ቀጥለውበታል ። ኢትዮጵያዊነታቸውን የካዱትም አላመለጡም ። በኢትዮጵያውያን ላይ ይጠንክር እንጂ ኤርትራውያንንም አፈሳው ይመለከታል ።

ስደተኞች አዲስ መታውቂያ ወረቀት የላቸውም የሚለው አልባሌ ሰበብ መሆኑን መረጃው ያላቸው ምንጮች ይገልጣሉ ። መታወቂያው ያላቸውም ቢሆን ከመንገላታትና ከመዘረፍ-መታፈስ አላመለጡም ። የወያኔ ሰላዮችም የስም ዝርዝር ይዘው የሚፈልጓቸውን ስደተኞች ያሳድዳሉ ። የበሺር አገዛዝ የሰብዓዊ መብት ጠላት እንደመሆኑ መጠን (በሰሞኑ በርካታ ነጻ ጋዜጦችን ዘግቶ ጋዜጠኞችንም አስሯል ) በእናቷ ኢትዮጵያዊና ክርስቲያን የሆነችውን ጥሏት የጠፋው አባትሽ ሱዳንና እስላም ነበር በሚል ሀይማኖትሽን ቀየርሽ ብሎ ለእሥር ከዳረጋት በኋላ መቶ ጅራፍና ሞት ፈርዶባታል ። ሳውዲ አረቢያ እንደሚያደርገው ሁል ሀይማኖት መቀየር በሞት ያስቀጣል ። የስምንት ወር ርጉዝ የሆነችውና ዬእናቷን ሀይማኖት ከልጅነቷ ጀምራ የተቀበለችው ይቺ ኢትዮጵያዊ ከሌላ ህጻን ልጇ ጋር ለቆሻሻው የሱዳን እስር ቤት ተዳርጋለች። እሷንም በተመለከተ የኢትዮጵያውያን እንቅስቃሴ ደካማ ነው። በዩጋንዳና ኬንያም እየማቀቁ ያሉ ጋዜጠኞችና ስደተኞች የዚህ ዝምታ ሰለባ ሆነዋል ። ስደተኞቹን ወደ ሌላ ሀገር ለማውጣት ከሚመለከታቸው ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያላቸው ደግሞ የእኛ ድርጅት አባል ካልሆንክ የሚል ቅድመ ሁኔታ ማቅረባቸውን የሚመለከታቸው እየገለጹ ናቸው ። ለሕይወታቸው የሚሰጉ ስደተኞች በሱዳን ፤ በኬንያ፤ በጅቡቲና ዩጋንዳ አሁንም አሉና በባዕድ ሀገር የሚኖሩ ዜጎች ዝምታ ወይም ለቀቅተኝነት መቆም ይገባዋል ። በሱዳን ኤምባሲና ቆንስላ ፊት ለፊት መሰለፍና ተቃውሞ ማሰማት፤ ስደተኞቹን ሊወስዱ የሚችሉትን ሀገሮች ስለ ችግሩ ማስረዳት፤ የተባበሩት መንግስት የስደተኛ ኮሚሽንን ስራውን ባለመስራቱ ማውገዝ ወዘተ ያስፈልጋል ።

በወያኔ ደብዛቸው የጠፋውን መርሳት ፤ የታገቱትና የታሰሩት የድርጅታችን አባሎች አይደሉም ብሎ መዘጋት፤ ባዕዳን የሚያነሷቸውን የእስረኞች ስም ብቻ ማንሳት፤ የሰብዓዊ መብትን ጉዳይ ለፖለቲካ ተገዢ ማድረግ ሀገርንም ወግንንም ይጎዳልና ባስቸኳይ መቆም ያለበት ነው ።

ስደተኛ ወገኖቻችንን እንታደግ!
ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!!

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.COM